- 3 -

የባዶነት ስሜትን በመሙላት ወደ ቤት መመለስ

ከዚያ ከመጀመርያው ቤታችን ተፈናቅለን፤ ከመነሻችን ርቀን ነው ያለነው። በጊዜ ሂደትና በተፈጠረ ከስተት ወደ ሌላ ዓለም መጥተናል። ወደ ትንሽ ዓለም። ከዚያኛው ዓለም (ከጀነት) በመለየታችን የሆነ አሳማሚ ነገር ውስጣችን ተፈጥሯል። ከአምላካችን ጋር በአካል የምንቀርብበት ቦታ አይደለም ያለነው። ወደፊትም በዐይናችን ላንመለከተው፣ በድምፅም ላናናግረው እንችላለን። ከጀነት እንዲወጣ እንደተደረገው እንደ አባታችን አደም (ዐ.ሰ.) ሁሉ ያንን ፍጹም የሆነ ውስጣዊ ሰላም ፈፅሞ መልሰን ላናገኘው እንችላለን።

ወዲህ መጥተናል፣ ወደ ምድር ወርደናል። ከአምላካችን ተለይተናናል። በዚያ መለያየት ውስጥ ህመም አለ። በውስጣችን ደምተናል፣ ተጎድተናል። ያ መለያየት ጠባሳን ትቶብን አልፏል። ለመጀመርያ ጊዜ የደማነው ያኔ ከጀነት ስንወጣ ነበር። ያ ከፈጣሪያችን የተለየንበት ሁኔታ እስከዘላለሙ ትልቅ ቁስል ትቶብን አልፏል። ከዚያ ጥልቅ ቁስል ጋር ነው ሁላችንም የተወለድነው። እያደግን ስንመጣ የዚያ ቁስል ህመም አብሮን በጥልቀት እያደገ ይመጣል። ግና ጊዜ በሄደ ቁጥር ከማገገሚያችንና ከመዳኛችን እየራቅን እየራቅን ሄደናል። ጥንተ ተፈጥሮአችን ከነበረው በሙሉ ልባችንና በመላ ሃሳባችን ወደ ጌታችን ከመቅረብ እየተዘናጋን መጥተናል።

በዚህ መልኩ ዓመታት ባለፉ ቁጥር፤ በመለያየቱ ከገጠመን የውስጥ ስብራት ለማገገም እና ለመጥጠገን በይበልጥ እየራቅንና ተስፋ እየቆረጥን እንመጣለን። በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ላይ ስንጥቃችንን የመሙላቱ ነገር እጅግ አጠያያቂ ነው። ሁላችንም በተለያየ መንገድ ወድቀናል። አንዳንዶቻችን በአደንዛዥ ዕፅ፣ ከፊሎቻችን በአልኮል መጠጥ። አንዳንዶቻችን ሰመመን ውስጥ ነው። በሞትና በሕይወት መካከል። አንዳንዶቻችን ለሥጋዊ ነገሮች ተሸንፈናል፤ ዝና እና ገንዘብ ያሸነፈንም ብዙዎች ነን። አንዳንዶቻችን ደግሞ በሥራችን ውስጥ ሰጥመን ጠፍተናል። ይህ ሁሉ በርግጥ ውድቀት ነው። ሽንፈት። መሰመርን መሳት።

አንዳንዶቻችን በሰዎች ጉዳይ ብቻ ተጠምደናል። በዚህም የተነሳ ራሣችን ረስተናል።

ነገር ግን በሕይወታችን ውስጥ የሚገጥመንን እያንዳንዱን ውድቀት፣ መሰናከል፣ እንቅፋትና ፈተና ለሆነ ዓላማ ብቻ ታስቦ የሆነ ቢሆንስ በምን እናውቃለን? ወደ ማንነታችን ሊመልሰን የተደረገ ቢሆንስ? እያንዳንዱ ማሸነፍ፣ እያንዳንዱ ማጣት፣ውበት፣ ውድቀት፣ አደጋ፣ ፈገግታ ... የተከሰተውና የሆነው ሁሉ በኛና በጌታችን መካከል በመግባት ዐይናችንን የጋረደውን ዓይነርግብ ለመግለጥና ከጌታችን ጋር ለማቀራረብ ቢሆንስ እንዴት ልናውቅ

እንችላለን? እኛን ተስፋ ወደ ቆረጥንበት ወደጥንተ ተፈጥሮአችን ለመመለስ ቢሆንስ?

የሆነው ነገር ሁሉ እንዲሆን የተፈቀደው እሱን (አምላካችን) ለማየት እንድንችል ቢሆንስ?

በሕይወት ውስጥ የሚያጋጥመን ነገር ሁሉ የሆነው ለሆነ ዓላማ እንደሆነ ማወቅ ይኖርብናል። ያ ዓላማ ይሳካ አሊያም ይደናቀፍ ዘንድ ምርጫው የኛ ነው። ለምሳሌ ውበትን እንውሰድ፤ አንዳንድ ሰዎች ውበት ፊት ለፊታቸው እያለ እንኳን ማስተዋል አይችሉም። ፀሐይ በምትጠልቅበት ጊዜ የሚታየውን በሚያምር ጫካ፣ አሊያም የብርቱካን ዛፍ መካከል እየተጓዙ የሚታየውን ውበት አያስተውሉም።

ሌሎች ደግሞ ውበትን ያያሉ። በውበትም መመሰጥ ይችላሉ። ቆም ብለው በማየት ወደ ውስጣቸው እንዲዘልቅ ይፈቅዳሉ። በርሱ መላ ሀሳባቸው ሊዋጥ ሁሉ ይችላል። ግና አድናቆታቸውና መመሰጣቸው እዚያው ላይ ያበቃል። የዚህ ዓይነቶቹ ልክ የጥበብ ሥራን እንደሚያደንቅ እና ስለ ጥበበኛው ግድ የማይሰጠው ሰው ናቸው። መጠየቅም አይፈልጉም። ማንነቱን ማወቅ አይሹም። የጥበብ ሥራው ብቻውን ጥበበኛውን ወክሎ የሚያስተላልፈው መልዕክት አለው። የጥበብ አፍቃሪው በሥራው ውበት ተማርኮ ቅቡን ብቻ የሚያይ ከሆነ መልዕክቱን የማይገነዘብ የጥበብ ሥራው እውነተኛ አላማውን አላሳካም ማለት ይቻላል።

ምድርን አጅበው የሚገኙ ነገራት በጠቅላላ- ፀሐይ፣ የሚወድቁ በረዶዎች፣ አብሪ ጨረቃና ከዋክብት፣ መሣጭ የሆኑት ባህርና ውቅያኖሶች ወዘተ የመፈጠራቸው ምክንያትና ዓላማ ይህችን ብቸኛ ምድር ለማስዋብ ብቻ አይደለም። የመፈጠራቸው ዓላማ ከዚያ ላቅ ያለ ነው። አላህ ሱ.ወ. በቁርአኑ ይህንን ሲናገርም እንዲህ ብሏል፡-

﴿ إِنَّ فِي خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَٱخْتِلَٰفِ ٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ لَءَايَٰتٍ لِّأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ ﴿١٩٠﴾ ٱلَّذِينَ يَذْكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمْ وَيَتَفَكَّرُونَ فِي خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَٰذَا بَٰطِلًا سُبْحَٰنَكَ فَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ﴾

«ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር ሌትና ቀንንም በመተካካት ለባለ አእምሮዎች በእርግጥ ምልክቶች አሉ። (እነርሱም) እነዚያ ቆመው፣ ተቀምጠውም፣ በጎኖቻቸው ተጋድመውም አላህን የሚያወሱ በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ፡- ጌታችን ሆይ! ይኽን በከንቱ አልፈጠርከውም፣ ጥራት ይገባህ፣ ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን፣ የሚሉ ናቸው።»

(ኣሊ ዒምራን፡ 190-191)

ይህ ሁሉ ውበት ጥቁምታ ምልክት ነው የመፈጠር ዓላማው። ለነዚያ ማስተዋል ለሚችሉት

እና ማስተንተን እና ጌታቸውን ማውሳትን አውሺ ለሆኑት ነው መልዕክቱ የሚገባው። ለነዚያ በየትኛውም የሕይወት አጋጣሚ ውስጥ ቢሆኑም፤ ቆመው፣ ተቀምጠውም ሆነ በጎናቸው በተጋደሙም ፈጣሪያቸውን አስታዋሽ ለሆኑት።

ስለሆነም ፀሐይ ስትጠልቅ ሁሉ በአስተውሎት መመልከት አለብን። በዙርያችን በምንመለከተው ነገር ውስጥ ያለውን መልዕክት መረዳት አለብን። ከዚያ የሰነ ሕይወት ቀለማት ውበት ባሻገር እውነተኛው ውበት መመልከት መቻል አለብን።የምንመለከተው ነገር የሆነ ነገር ነፀብራቅ ነው። ምልክት ይሠጠናል።

ከዋክብት በጥልቀት ልብ ብለን ልንመለከት ይገባል። ዛፎችን፣ የበረዶ ግግሩን፣ ተራራውንም እንዲሁ። እነኘህ ሁሉ የሚነበቡ ናቸው። ከኋላቸው ትልቅ መልዕክት ያዘሉ ናቸው። መልዕክቱን ማንበብ አለመቻል፤ በተዋበ ጠርሙስ ውስጥ መልዕክት እንደሚፈልግ ሰው ነው። ያውም በማይከፈትና በተዘጋ ጠርሙስ ውስጥ።

ስለሆነም የከዋክብትን መልዕክትና ምስጢር ለማወቅ መጣር አለብን። በርግጥ ምልክቶች ናቸው። የምን ምልክት ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። ወደሆነ ነገር ያመለክታሉ። ወደ ኃያሉ አላህ። ወደ ታላቁ አላህ! ወደ ድንቅ ሥራው። ኃይሉንና ችሎታውን ነው የሚያሳዩን። ስለሆነም እሱ የፈጠራቸውን ነገሮች ማጥናት መገንዘብና ማሰላሰል ይኖርብናል። እዚህ ላይ ማቆም የለብንም። በውበቱ መስጠም ሳይሆን ከውበቱ ጀርባ ያለውን ኃያልና ታላቅ ፈጣሪ ማወቅ ይኖርብናል። ምንኛ ታላቅ የሆነ ጌታ ነው!! ውብ የሆነ ፈጣሪ።

በስተመጨረሻ ይህንን ግንዛቤ እናገኛለን:-

﴿ رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَٰذَا بَاطِلًا سُبْحَانَكَ فَقِنَا عَذَابَ النَّارِ ﴾

«ጌታችን ሆይ! ይኽን በከንቱ አልፈጠርከውም፤ ጥራት ይገባህ።»

(ኣሊ ዒምራን: 191)

ሁሉም ነገር ለሆነ ዓላማ ነው የተፈጠረው። በምድርም ሆነ በሰማይ፣ በኔ ውስጥም ሆነ በናንተ ውስጥ አንድም ነገር ያለ ዓላማ የተፈጠረ የለም። በሕይወታችሁ ውስጥ ማጣትም ይሁን ማግኘት፣ ደስታም ይሁን ሐዘን ያለ አንዳች ዓላማ የሚከሰት ነገር አይኖርም። ስለሆነም በፀሐይ፣ በጨረቃ እና በሰማይ ጠርሙስ ውስጥ ያለውን መልእክት ማንበብ እና መረዳት ይኖርብናል። በሕይወታችን ውስጥ የሚከሠቱትን መልዕክቶችም እንዲሁ።

ምልክቶች ሁሌም በዙርያችን አሉ። ሁሌም ጌታችን እንዲያናግረን እንፈልጋለን። ግን እነኚህን ምልክቶች አናስተውልም። በሁሉም ነገር ውስጥ አሉ። በነርሱ አማካይነት አላህ ሁሌም እያናገረን መሆኑ ልናውቅ ይገባል። ሁሌም እንዳናገረን ነው። ቁም ነገሩ እኛ

እናዳምጣለን ወይ የሚለው ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَقَالَ ٱلَّذِينَ لَا يَعْلَمُونَ لَوْلَا يُكَلِّمُنَا ٱللَّهُ أَوْ تَأْتِينَآ ءَايَةٌ ۗ كَذَٰلِكَ قَالَ ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِهِم مِّثْلَ قَوْلِهِمْ ۘ تَشَٰبَهَتْ قُلُوبُهُمْ ۗ قَدْ بَيَّنَّا ٱلْءَايَٰتِ لِقَوْمٍ يُوقِنُونَ ﴾

"እነዚያም የማያውቁት አላህ አያናግረንም ናሮአልን? ወይም (ለእውነተኝነትህ) ታምር አትመጣልንም ናሮአልን? አሉ። እንደዚሁ እነዚያ ከነሱ በፊት የነበሩት እንደ ንግግራቸው ብጤ ብለዋል። ልቦቻቸው (በክህደት) ተመሳሰሉ። ለሚያረጋግጡ ህዝቦች አንቀፃችን በእርግጥ አብራርተናል።"

(አል-በቀራህ : 118)

በሕይወታችን ውስጥ ከሚከሰትብን እና ከሚሆንብን ነገር ተሻግረን መመልከት ከቻልን ያኔ በኛ ላይ የሚከሰትብን ነገር ሁሉ ስኬትም ይሁን ውድቀት ዓላማ እንዳለው እንገነዘባለን። በነርሱ አማካይነት አላህን እናያለን። ዓላማውንም እንገነዘባለን። የምንወደው ነገር የተከሠተ እንደሆነ ዓላማው ምን እንደሆነ ለማወቅ እንሞክር። ያለ ዓላማ የተከሠተ ምንም ነገር የለምና። በማስተንተን እንመልከተው። አላህ (ሱ.ወ.) በሰጠን ነገር ውስጥ ዓላማው ምን እንደሆነ እንመልከት። ምንድነው መሠረታዊ ዓላማው? በክስተቱ በኩል ሊያሳየን የፈለገው ነገር ምንድነው?

የምንጠላው አሊያም የሚጎዳን ነገር የተከሠተብን እንደሆነም እንዲሁ ሚስጢሩን እንመራመር። በህመሙ ውስጥ በሚፈጠረው ስሜት ተደናግረን እንዳናጣው እንጠንቀቅ። በጥልቀት መመልከት ይኖርብናል። ጠርሙሱ የያዘውን መልእክቱን ለማግኘት እንሞክር። ዓላማውን ለማወቅ እንጣር። ወደ ብርሃኑ እንዲመራን መንገዱን እንክፈትለት። ወደርሱ ለመቅረብ በሚረዳን መልኩ እንገንዘብ።

በዲን መንሸራተት አሊያም ውድቀት ከሆነም ሸይጣን እንዳያታልልህ ተጠንቀቅ።መንሸራተትህ የርሱን እዝነት በማሰብ ይበልጥ ወደ አላህ ለመቅረብ ተጠቀምበት።የርሱ ምህረት እንደሆነ በጥልቀት ለማሰብ ለራስህ መንገድ ክፈት። ከወንጀልና ከራስህ ጥፋት ይጠብቅህ ዘንድም እዝነቱን ከጅል።

ችግርህ የማይቀረፍ ዓይነት ቢሆን እንኳን ተስፋ አትቁረጥ። አስታውስ "አል-ፈታሕ" የሆነው አላህ ለባሮቹ በየትኛውም ጉዳይ ላይ የተዘጋን ነገር ሁሉ የሚከፍት ነው። ከባድ ማዕበል ቢከሥት እንኳን ለመትረፍ እንጂ ለመስጠም ራስህን አዘጋጅተህ አትጠብቅ። እሱ ባርያውን ከከባድ ማዕበል እንዴት ሊያድን እንደሚችል ዓለም ላይ ምስክር ቢጠፋ እንኳን እኛው ምስክር እንሁን። በመጨረሻም ፍጥረተ ዓለሙ ሁሉ እንደሚጠፋና እርሱ ብቻውን እንደሚቀር አትርሳ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ እያለ የሚጠይቅበትንም ቀን

አስታውስ፡-

﴿ يَوْمَ هُم بَٰرِزُونَ لَا يَخْفَىٰ عَلَى ٱللَّهِ مِنْهُمْ شَىْءٌ ۖ لِّمَنِ ٱلْمُلْكُ ٱلْيَوْمَ ۖ لِلَّهِ ٱلْوَٰحِدِ ٱلْقَهَّارِ ﴾

«እነርሱ (ከመቃብር) በሚወጡበት ቀን፣ በአላህ ላይ ከእነርሱ ምንም ነገር አይደበቅም፤ ንግስናው ዛሬ ለማን ነው? (ይባላል)። ለአሸናፊው፣ ለአንዱ አላህ ብቻ ነው፤ (ይባላል)።» (ጋፊር፡ 16)

ንግስናው የማን ነው ዛሬ? ... ስለሆነም ይህንኑ በዚህ ምድራዊ ሕይወታችን ጥቂትም ቢሆን ለመመስከር እንሞክር። ገዥነቱና የበላይነቱ የማን ነው?። እኛን የማዳን ኃይልና ሥልጣን ያለው ማነው? ማን ነው የሚፈውሰን? ልባችንን የሚጠግንልን ማነው? ሲሳያችንን የሚለግሰን ማነው? የምንሸሸው ወደ ማንነው? እኮ ከአላህ ውጭ ወደ ማን? አሸናፊነትና የበላይነት ለማነው? ዛሬስ ቢሆን ንግስናው የማነው?

"ሊልላሂል ዋሒዲል ቀሃር" "ለአንድዬው!! ለአሸናፊው ለአላህ ነው!!" የምንሸሸባቸው ሁሉ ይሸነፋሉ። እሱ ግን የማይሸነፍ የሆነ ጌታ ነው። መጠጊያችንና መሸሻችን የምንላቸው አይጠቅሙንም። እሱ ብቻ ነው ውስጣችን የሚሞላው። ከሱ ውጭ የሚጠግነን፣ የሚፈውሰን፣ ልባችንን፣ ነፍሳችንና አዕምሯችንን የሚሞላልን ማንም የለም።

ስለሆነም በዚሁ መንገድ ነው መጓዝ ያለብን። ያ መንገድ ነው ቀድሞ ወደነበርበት ጀነት የሚያደርሰን። ከሱ ወዴትም መሸሽ አንችልም። ከሁሉም በላይ እሱ ያስፈልገናል። ሁላችንም ተመሳሳይ ነገር ነው የምንፈልገው። መረጋጋትና መደሠት። እንደገና "ቤታችን ይህ ነው!" ማለት።

ቤታችን ጀነት ነው።